# ለላንካስተርና ለፓልምዴል ቤተክርስቲያንና መሪዎች ምን መጸለይ አለብን

# What to Pray for the Church and Leaders of Lancaster and Palmdale

ጌታ: "እነርሱን ወክላችሁ በፊቴ ራሳችሁን ብታኖሩ፤ ለትልቁ ዘላለማዊ ፈቃዴና አላማዬ እንዲታወቅና እንዲገነዘብ በግላችሁ ወደ እኔ ብትመጡና ከፊቴ ብትቆሙ፥ ከዛ እኔ የሚየቃጥል መንፈስ ጥምቀት (ኢሳይያስ4፥4) በእናንተ ላይ አፈስሳለሁ እና የሚልክያስ 3፥1-5 ፍጻሜም ለእናንተ ይሆንላችኋል።

እናንተ ከእኔ ጋር በልብ አንድ ትሆናላችሁ እኔም በምድረበዳ ፏፏቴዎችን እከፍታለሁ። የሞገስንና የማንባትን መንፈስ ወደፊት አፈስሳለሁና ደረቅ ቦታዎቻችሁ የምንጮች መሬት ይሆናሉ። እናንተ የመሻቴ እቃ ትሆናላችሁ እኔም በረካው(በተደሰተው) ልባችሁ እደሰታለሁ።" አለ።

1. <u>**በክርስቶስ**</u> (ለሙሽራው በቅድስና ውበት የተዘጋጀች ሙሽራ) <u>**የእግዚአብሔር ዘላለማዊ አላማ እንዲገለጥ(ጽ)።**</u>

   ***ራእይ*** **19:7** "የበጉ ሰርግ ስለ ደረሰ <u>ሚስቱም ራስዋን ስላዘጋጀች</u> ደስ ይበለን ሐሤትም እናድርግ ክብርንም ለእርሱ እናቅርብ።"

   **ቆላስያስ 1:28** "<u>እኛም በክርስቶስ ፍጹም የሚሆን ሰውን ሁሉ እናቀርብ ዘንድ</u> ሰውን ሁሉ እየገሠጽን ሰውንም ሁሉ በጥበብ ሁሉ እያስተማርን የምንሰብከው እርሱ(ኢየሱስ ክርስቶስ) ነው።"

   **ማቴዎስ 25:10** "(ለመብራታቸው ዘይት) ሊገዙም በሄዱ ጊዜ(ሰነፎቹ ደናግላን/ቆነጃጅት) ሙሽራው መጣ፥ ተዘጋጅተው የነበሩትም ከእርሱ ጋር ወደ ሰርግ ገቡ፥ ደጁም ተዘጋ።" <u>ቅድስት ሙሽራ እንድትኖር የሆነውን የእግዚአብሔርን ጥሪ በማያውቁ ወይም በማይረዱ መካከል መቀስቀስ(መነቃቃት) እንዲኖር ጸልዩ።</u>

   **2ኛ ቆሮንቶስ 11:2-3** "በእግዚአብሔር ቅንዓት እቀናላችኋለሁና፥ <u>እንደ ንጽሕት ድንግል እናንተን ለክርስቶስ ላቀርብ</u> ለአንድ ወንድ አጭቻችኋለሁና፤ ነገር ግን እባብ በተንኮሉ ሔዋንን እንዳሳታት፥ አሳባችሁ ተበላሽቶ ለክርስቶስ ከሚሆን ቅንነትና ንጽሕና ምናልባት እንዳይለወጥ ብዬ እፈራለሁ።"

   <u>ሁሉም ቅዱሳን ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደሚሆን ንጹሕ ፍቅር ተመልሰው ይመጡ ዘንድ፥ እና ለእርሱ እንደተዘጋጁ ንጹሕ ድንግሎች ሆነው ይኖሩ ዘንድ ጸልዩ።</u>

2. <u>**የኢየሱስ ምስክርነት መልሶ እንዲያዝ (The testimony of Jesus to be recaptured)**</u>

   **ኢዩኤል 2:17** ". . .ከአሕዛብ መካከል:- አምላካቸው ወዴት ነው? ስለ ምን ይላሉ?" <u>ኢየሱስ ክርስቶስ በከፍታ ይሞገስ ዘንድ የእግዚአብሔር ክብር እና የተገለጠው ኃልውናው ፈውሱም፣ ማዳኑም፣ አዳኝ ፍቅሩና ኃይሉም በቤተክርስቲያኖች ውስጥ እንዴ በድጋሜ እንዲታይ ጸልዩ።</u>

   በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ ባለችው ቤተክርስቲያን "ዓለም" የእግዚአብሔርን ክብር አይቷል። **የሐዋርያት ሥራ 5:16** "ደግሞም በኢየሩሳሌም ዙሪያ ካለችው ከተማ ድውያንንና በርኵሳን መናፍስት የተሣቀዩትን እያመጡ ብዙ ሰዎች ይሰበሰቡ ነበር፤ ሁሉም ይፈወሱ ነበር።" <u>ሸለቆአችን ኢየሱስን በተግባር ላይ ሆኖ እንዲያየው ጸልዩ።</u>

## 3. <u>በቤተክርስቲያን ምክንያት የጌታ ስም በአሕዛብ መካከል ከእንግዲህ ወዲያ እንዳይሰደብ</u>

<u>በሽለቆአችን ውስጥ ያለችው ቤተክርስቲያን በመሐከላችን ባለው በኢየሱስ ምክንያት እግዚአብሔርን እንድታከብረው ጸልዩ።</u>

**ማርቆስ 2:12** ተነሥቶም (ከሽባነት የተፈወሰው ሰውዬ) ወዲያው አልጋውን ተሸክሞ በሁሉ ፊት ወጣ፥ ስለዚህም ሰዎች ሁሉ ተገረሙና። እንዲህ ያለ ከቶ አላየንም ብለው እግዚአብሔርን አከበሩ።

## 4. <u>የመንፈስ ቅዱስና የእሳት ጥምቀት የንስሐን ጥምቀት ሲከተል፤</u>

**ትንቢተ ኢሳይያስ 6:1-7** ንጉሡ ዖዝያን በሞተበት ዓመት እግዚአብሔርን በረጅምና ከፍ ባለ ዙፋን ላይ ተቀምጦ አየሁት፥ የልብሱም ዘርፍ መቅደሱን ሞልቶት ነበር። 2፤ ሱራፌልም ከእርሱ በላይ ቆመው ነበር፥ ለእያንዳንዱም ስድስት ክንፍ ነበረው፤ በሁለት ክንፍ ፊቱን ይሸፍን ነበር፥ በሁለቱም ክንፍ እግሮቹን ይሸፍን ነበር፥ በሁለቱም ክንፍ ይበር ነበር። 3፤ አንዱም ለአንዱ። ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፤ ምድር ሁሉ ከክብሩ ተሞልታለች እያለ ይጮኽ ነበር።

4፤ የመድረኩም መሠረት ከጭዋኺው ድምፅ የተነሣ ተናወጠ፥ ቤቱንም ጢስ ሞላበት። 5፤ እኔም። ከንፈሮቼ የረከሱብኝ ሰው በመሆኔ፥ ከንፈሮቻቸውም በረከሱባቸው ሕዝብ መካከል በመቀመጤ ዓይኖቼ የሠራዊትን ጌታ ንጉሡን እግዚአብሔርን ስለ አዩ ጠፍቻለሁና ወዮልኝ! አልሁ።

6፤ ከሱራፌልም አንዱ እየበረረ ወደ እኔ መጣ፥ በእጁም ከመሠዊያው በጕጠት የወሰደው ፍም ነበረ። 7፤ አፌንም ዳሰሰበትና። እነሆ፥ ይህ ከንፈሮችህን ነክቶአል፤ በደልህም ከአንተ ተወገደ፥ ኃጢአትህም ተሰረየልህ አለኝ።

ኢሳይያስ እንደተለማመደው ንስሐን በሚያመጣ በቅድስናው ውበት ጌታ ራሱን እንዲያስታውቅ ጸልዩ።

**የሐዋርያት ሥራ 19:18-20** "አምነውም ከነበሩት እጅግ ሰዎች ያደረጉትን እየተናዘዙና እየተናገሩ ይመጡ ነበር።

19 ከአስማተኞችም ብዙዎቹ መጽሐፋቸውን ሰብስበው በሰው ሁሉ ፊት አቃጠሉት፤ ዋጋውም ቢታሰብ አምሳ ሺህ ብር ሆኖ ተገኘ። 20 እንዲህም የጌታ ቃል በኃይል ያድግና ያሸንፍ ነበር።" አንዱ ብር 20$ ቢሆን፥ 1 ሚሊዮን$$ ዋጋ ያላቸው ቆሻሻ መጽሐፍቶች ተቃጠሉ!!

<u>እግዚአብሔር ኃጢአትን ማሳየት(conviction of sin) በጣም በትልቁ እንዲልክ እና እኛም በጌታ ፊት ለቅድስና የሚሆን በቤተክርስቲያን ሁሉ በሕይወታችን(በኑሮአችን) በብዛት ንስሐ እንዲኖረን</u> (ብዙዎች ኃጢአታቸውን ተናዘውና ኃጢአትን ትተው በንስሐ ሕይወት በመድኃኒታችን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እንድንኖር) <u>ጸልዩ።</u>

**የሐዋርያት ሥራ 2:1-4** በዓለ ኀምሳ የተባለውም ቀን በደረሰ ጊዜ፥ ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው አብረው ሳሉ፥ 2 ድንገት እንደሚነጥቅ ዓውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣ፥ ተቀምጠው የነበሩበትንም ቤት ሁሉ ሞላው። 3 <u>እንደ እሳትም የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩአቸው፤ በያንዳንዳቸውም ላይ ተቀመጡባቸው። 4 በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው</u>፥ መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደ ሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር።

<u>በጣም ኀያል የመንፈስ ቅዱስና የእሳት ጥምቀት</u> በሸለቆአችን ውስጥ ባሉ ቤተክርስቲያኖች ላይ እንዲመጣ ጸልዩ።

## 5. <u>እግዚአብሔርን መፍራት እንዲሰጥ (The fear and terror of the Lord to be imparted)</u>

**መጽሐፈ ምሳሌ 9:10** የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው፤ ቅዱሱንም ማወቅ ማስተዋል ነው።

**ትንቢተ ኤርምያስ 32:40** . . . ከእኔም ዘንድ ፈቀቅ እንዳይሉ መፈራቴን በልባቸው ውስጥ አኖራለሁ።

**የሐዋርያት ሥራ 2:43** ነገር ግን በሰው ሁሉ ፍርሀት ሆነ፤ በሐዋርያትም እጅ ብዙ ድንቅና ምልክት ተደረገ። (የእግዚአብሔር ክብር እውነተኛ እግዚአብሔርን መፍራት ሁል ጊዜ ይከተላል)

**የሐዋርያት ሥራ 9:31** . . . አብያተ ክርስቲያናት በሰላም ኖሩ ታነጹም፤ በእግዚአብሔርም ፍርሃትና በመንፈስ ቅዱስ መጽናናት እየሄዱ ይበዙ ነበር።

**2ኛ ቆሮንቶስ 5:10-11** መልካም ቢሆን ወይም ክፉ እንዳደረገ፥ እያንዳንዱ በሥጋው የተሠራውን በብድራት ይቀበል ዘንድ ሁላችን በክርስቶስ በፍርድ ወንበር ፊት ልንገለጥ ይገባናልና። 11 እንግዲህ የጌታን ፍርሃት አውቀን ሰዎችን እናስረዳለን ለእግዚአብሔር ግን የተገለጥን ነን፤ በሕሊናችሁም ደግሞ የተገለጥን እንደ ሆንን ተስፋ አደርጋለሁ።

## 6. <u>የእግዚአብሔር ክብር ጥማታችን እንዲሆን</u>

**መጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልዕ 5:13-14** መለከቱንም የሚነፉ መዘምራኑም በአንድነት ሆነው እግዚአብሔርን እያመሰገኑና እያከበሩ። እግዚአብሔር ቸር ነውና፥ ምሕረቱም ለዘላለም ነውና እግዚአብሔርን አመስግኑ እያሉ በአንድ ቃል ድምፃቸውን ወደ ላይ ከፍ አድገው በመለከትና በጸናጽል በዜማም ዕቃ ሁሉ እግዚአብሔርን ባመሰገኑ ጊዜ፥ <u>ደመናው የእግዚአብሔርን ቤት ሞላው</u>። 14፤ <u>የእግዚአብሔርም ክብር የእግዚአብሔርን ቤት ሞልቶት ነበርና ካህናቱ ከደመናው የተነሣ መቆምና ማገልገል አልተቻላቸውም።</u>

**2ኛ ተሰሎንቄ 2:14** ለዚህም የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን <u>ክብር ለማግኘት</u> <u>በወንጌላችን ጠራችሁ</u>።

**2ኛ ቆሮንቶስ 3:7-8** ዳሩ ግን የእስራኤል ልጆች ስለዚያ ስለ ተሻረው ስለ ፊቱ ክብር የሙሴን ፊት ትኩር ብለው መመልከት እስኪሳናቸው ድረስ፥ ያ በፊደላት በድንጋዮች ላይ የተቀረጸ የሞት አገልግሎት (ሕጉ) በክብር ከሆነ፥ 8 <u>የመንፈስ አገልግሎት (አዲስ ኪዳን) እንዴት ይልቅ በክብር አይሆንም?</u>

## 7. <u>እግዚአብሔር የእርሱን ሕልውና(ፊቱን) የሚወድዱ ሰዎች እንዲኖሩት</u>

**መዝሙር 16:11** የሕይወትን መንገድ አሳየኸኝ፤ <u>ከፊትህ ጋር ደስታን አጠገብኸኝ</u>፥ በቀኝህም የዘላለም ፍሥሐ አለ።

**ኤፌሶን 2:20-22** "በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል፥ የማዕዘኑም ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤ 21 በእርሱም ሕንጻ ሁሉ እየተጋጠመ በጌታ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንዲሆን ያድጋል፤ 22 <u>በእርሱም እናንተ ደግሞ ለእግዚአብሔር መኖሪያ ለመሆን በመንፈስ አብራችሁ ትሠራላችሁ።"</u>

## 8. <u>ያ በግዴለሽ ባህሪ የሚመጣ ተግባረ ልክስክስነት እና ድብልቅ ይወገድ (That compromise and mixture be removed)</u>

**<u>ማርቆስ 12:30</u>** አንተም በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹምም አሳብህ በፍጹምም ኃይልህ ጌታ አምላክህን ውደድ የምትል ናት። ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት።

**ራእይ 3:14-21** በሎዶቅያም ወዳለው ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ። አሜን የሆነው፥ የታመነውና እውነተኛው ምስክር፥ በእግዚአብሔርም ፍጥረት መጀመሪያ የነበረው እንዲህ ይላል። 15 <u>በራድ ወይም ትኩስ እንዳይደለህ</u> ሥራህን አውቃለሁ። <u>በራድ ወይም ትኩስ ብትሆንስ መልካም በሆነ ነበር</u>። 16 እንዲሁ ለብ ስላልህ በራድም ወይም ትኩስ ስላልሆንህ ከአፌ ልተፋህ ነው። 17 ሀብታም ነኝና ባለጠጋ ሆኜአለሁ አንድም ስንኳ አያስፈልገኝም የምትል ስለ ሆንህ፥ ጐስቋላና ምስኪንም ድሀም ዕውርም የተራቆትህም መሆንህን ስለማታውቅ፥ 18 ባለ ጠጋ እንድትሆን በእሳት የነጠረውን ወርቅ፥ ተጐናጽፈህም የራቁትነትህ ኃፍረት እንዳይገለጥ ነጭ ልብስን፥ እንድታይም ዓይኖችህን የምትኳለውን ኵል ከእኔ ትገዛ ዘንድ እመክርሃለሁ። 19 እኔ የምወዳቸውን ሁሉ እገሥጻቸዋለሁ እቀጣቸውማለሁ፤ እንግዲህ ቅና ንስሐም ግባ። 20 እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ፤ ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ፥ ወደ እርሱ እገባለሁ ከእርሱም ጋር እራት እበላለሁ እርሱም ከእኔ ጋር ይበላል። 21 እኔ ደግሞ ድል እንደ ነሣሁ ከአባቴም ጋር በዙፋኑ ላይ እንደተቀመጥሁ፥ ድል ለነሣው ከእኔ ጋር በዙፋኔ ላይ ይቀመጥ ዘንድ እሰጠዋለሁ።

**1ኛ ዮሐንስ 2:15-17** ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ፤ በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት ስለ ገንዘብም መመካት ከዓለም ስለ ሆነ እንጂ ከአባት ስላልሆነ፥ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም። 17 ዓለሙም ምኞቱም ያልፋሉ፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ግን ለዘላለም ይኖራል።

**ያዕቆብ 4:4** አመንዝሮች ሆይ፥ ዓለምን መውደድ ለእግዚአብሔር ጥል እንዲሆን አታውቁምን? እንግዲህ የዓለም ወዳጅ ሊሆን የሚፈቅድ ሁሉ የእግዚአብሔር ጠላት ሆኖአል።

## 9. <u>ልቦች የእውነትና ሙሉበሙሉ ወደ እርሱ ዞረው እንዲመለሱ</u>

**ኢዩኤል 2:12** “አሁንስ፥ ይላል እግዚአብሔር፥ በፍጹም ልባችሁ፥ በጾምም፥ በልቅሶና በዋይታ ወደ እኔ ተመለሱ።”

**ኤርምያስ 3:10** “በዚህም ሁሉ አታላይቱ ይሁዳ በሐሰት እንጂ በፍጹም ልብዋ ወደ እኔ አልተመለሰችም።” ይላል እግዚአብሔር።

**ኤርምያስ 24:7** እኔም እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ የሚያውቅ ልብ እሰጣቸዋለሁ፤ በፍጹምም ልባቸው ወደ እኔ ይመለሳሉና ሕዝብ ይሆኑኛል እኔም አምላክ እሆናቸዋለሁ።

## 10. <u>እርሱን ለማወቅ ጥልቅ ፍላጎት በውስጣችን እርሱ እንዲቀጣጠል (That He burn within us a deeper longing to know Him)</u>

**መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን 1:4** ሳበኝ፥ (ጸልዩ ‘ጌታ ሆይ፥ ወደ አንተ ሳበኝ’ )

**ፊልጵስዩስ 3:10-12** እርሱንና የትንሣኤውን ኃይል እንዳውቅ፥ በመከራውም እንድካፈል፥ ወደ ሙታንም ትንሣኤ ልደርስ ቢሆንልኝ፥ በሞቱ እንድመስለው እመኛለሁ። 12 አሁን እንዳገኘሁ ወይም አሁን ፍጹም እንደ ሆንሁ አይደለም፥ ነገር ግን ስለ እርሱ በክርስቶስ ኢየሱስ የተያዝሁበትን ያን ደግሞ እይዛለሁ ብዬ እፈጥናለሁ።

**ዮሐንስ 17:20-21** “ሁሉም አንድ ይሆኑ ዘንድ፥ ከቃላቸው የተነሣ በእኔ ስለሚያምኑ ደግሞ እንጂ ስለ እነዚህ ብቻ አልለምንም፤ አንተ እንደ ላክኸኝ ዓለም ያምን ዘንድ፥ አንተ፥ አባት ሆይ፥ በእኔ እንዳለህ እኔም በአንተ፥ እነርሱ ደግሞ በእኛ አንድ ይሆኑ ዘንድ እለምናለሁ።”

11. <u>የጌታ ትልቅ ሸክም በመሪዎች ላይ ትኩስ መለቀቅ እንዲመጣ (That a fresh release of the Lord's great burden come upon leaders)</u>

**2ኛ ቆሮንቶስ 11:27-28** በድካምና በጥረት ብዙ ጊዜም እንቅልፍ በማጣት፥ በራብና በጥም ብዙ ጊዜም በመጦም፥ በብርድና በራቁትነት ነበርሁ። 28 የቀረውንም ነገር ሳልቆጥር፥ ዕለት ዕለት የሚከብድብኝ የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ አሳብ ነው።

**2ኛ ጢሞቴዎስ 2:10** ስለዚህ እነርሱ ደግሞ በክርስቶስ ኢየሱስ ያለውን መዳን ከዘላለም ክብር ጋር እንዲያገኙ ስለ ተመረጡት በነገር ሁሉ እጸናለሁ።

<u>ሁሉም መሪዎች ለእግዚአብሔር ሕዝብ "ጥልቅ አሳብ" እንዲኖራቸው፥ እናም በዚህ ምክንያት፥ ለእነርሱ(ለእግዚአብሔር ሕዝብ) ብለው ሁሉንም ነገሮች እንዲቋቋሙ(እንዲጸኑ) ጸልዩ።</u>

12. <u>የሚወቅሰው መንፈስ በልቦች ላይ እንዲመጣ፥ እና በስብከትና በትምህርትም ወደ ፊት እንዲመጣ (The Spirit of conviction to come upon hearts, and to come forth in preaching and teaching)</u>

**የሐዋርያት ሥራ 2:36-37** አለ። እንግዲህ ይህን እናንተ የሰቀላችሁትን ኢየሱስን እግዚአብሔር ጌታም ክርስቶስም እንዳደረገው የእስራኤል ወገን ሁሉ በእርግጥ ይወቅ። 37 <u>ይህንም በሰሙ ጊዜ ልባቸው ተነካ</u>፥ ጴጥሮስንና ሌሎችንም ሐዋርያት። ወንድሞች ሆይ፥ ምን እናድርግ? አሉአቸው።

**ዮሐንስ ወንጌል 16:8** እርሱም(መንፈስ ቅዱስ) መጥቶ ስለ ኃጢአት ስለ ጽድቅም ስለ ፍርድም ዓለምን ይወቅሳል፤

13. <u>ለሕዝቡ እውነተኛ ምጥ ከሰማይ እንዲለቀቅ</u>

**ገላትያ 4:19** ልጆቼ ሆይ፥ ክርስቶስ በእናንተ እስኪሣል ድረስ ዳግመኛ ስለ እናንተ ምጥ ይዘኛል።

**ኢሳይያስ 66:8** ከቶ እንዲህ ያለ ነገር ማን ሰምቶአል? እንዲህስ ያለ ነገር ማን አይቶአል? በውኑ አገር በአንድ ቀን ታምጣለችን? ወይስ በአንድ ጊዜ ሕዝብ ይወለዳልን? ጽዮን እንዳማጠች ወዲያው ልጆችዋን ወልዳለችና።

14. <u>ሙሽራዋ እርሷን ዝግጁ እንዲያደርጋት ለበጉ እንድትፈቅድለት እና እርሷም ራሷን ለእርሱ ዝግጁ እንድታደርግ። (That the bride will allow the Lamb to make her ready and she will make herself ready for Him.)</u>

**ራእይ 19:7** የበጉ ሰርግ ስለ ደረሰ <u>ሚስቱም ራስዋን ስላዘጋጀች</u> ደስ ይበለን ሐሤትም እናድርግ ክብርንም ለእርሱ እናቅርብ።

**ሉቃስ 1:38** ማርያምም። እነሆኝ የጌታ ባሪያ <u>እንደ ቃልህ ይሁንልኝ</u> አለች። መልአኩም ከእርስዋ ሄደ።

ጊዜው እንዴት አጭር እንደሆነ የክርስቶስ አካል መገለጥ እንዲኖራት፤ እኛም "ዘመኑን(ሰዓቱን/ጊዜውን) እንድንዋጅ" እና እርሱ እንዲመራን፣ እንዲቀርፀን እና ለመልካም ፈቃዱና ለክብሩ እቃዎች እንዲያደርገን እየፈቀድንለት ሁላችንም ራሳችንን ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሙሉ በሙሉ እንድናስገዛ(እንድንሰጥ) <u>ጸልዩ</u>።

http://www.baptizingfire.com , http://fireofgodservants.blogspot.com/ , http://www.thelordshour.com , http://www.choothomas.org , http://www.jesusministries.org/ , http://www.angeltv.org , http://www.Billygraham.org , http://free.messianicbible.com/ , http://www.levitt.tv/ ,

http://www.divinerevelations.info/amharic , http://www.heavenvisit.com , http://www.tribulation-now.org , http://www.voe.org/ , http://www.sidroth.org , http://repentandpreparetheway.org/ , http://www.shekinahworship.com/ , http://www.theblazingholyfire.com/ , http://www.thelastreformation.com , http://www.bobjones.org/ , http://www.be4thefire.com/

http://www.annarountree.com/ , http://www.beyondthephysicalrealm.com , http://www.shreveministries.org , http://www.blogtalkradio/tribulation-now , http://www.blogtalkradio/thelordshour, http://www.blogtalkradio.com/discoveringthetruth

ክብር፥ ኃይል፥ በረከት፥ ምስጋና፥ ጥበብ፥ ማዳን፥ ቅድስና፥ ውዳሴ፥ አምልኮ እጅግ በከበረ ቅዱስ ቡሩክ ዙፋኑ ላይ ላለ የእስራኤል ኃያል አምላክ የሠራዊት ጌታ፥ አንድ አምላክ ለሆነ ለእግዚአብሔር አብ ለእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ለመንፈስ ቅዱስ ይሁን አሜን። ማራናታ ጌታ የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ የአብ ቃል የአብ ልጅ ቶሎ ና። ሃሌ ሉያ ክብር ለኢየሱስ ክርስቶስ ሃሌሉያ

ሊያደርግ የሚገባውን ያደረገ፥ የማይጠቅም ባሪያ ተረኀመው። **ሃሌ ሉያ**